# ሽምግልና ! !

በአገር አፍቃሪ ወንድማችሁ ከአሜሪካ
Feb 13, 2009

ሽምግልና በኢትዮጲያ ታሪክ ዉስጥ የተጣላ የሚታረቅበት፣ የተለያየ የሚገናኝበት፣ ደም እንኳን ሳያቀር የሚደርቅበት ዕርቅ የሚሰፍንበት ታላቅ ባህላዊ መሣሪያ ሆኖ ሲያገልግል ቆይቷል። በተለይ በሕግና በደንብ መፍቴ የሌላቸዉ ጉዳዮች በሽምግልና ዕልባት ስለሚያስገኙ አንቱ የሚባሉ ዉጤቶችን አስመዝግቧል፡፡ ዛሬ ግን በዘመነ ወያኔ በተለይም ዘመናዊ ፖለቲከኛ ነን የሚሉ ክፍሎች ከዚያ በተለየ መልኩ የሕዝቡን ትግል ለመበታተንና ለማሽመድመድ እየተጠቀሙበት ይገኛሉ፡፡ ገዥወቻችን ኮምኒዝም ወልዶ ኮምኒዝም እንደ አፈራቸዉ አድርገዉ ሲለፍፉ የቆዩ ([1] end of history/cold war) ጠባብ እና ዘረኛ ሆነዉ ሳለ ከዓለም ከበርቴ ጋር ለመቀላቀል ባላቸዉ ጽኑ ፍላጎት ምክንያት አቅጣጫቸዉን አስተካክለዉ (exit strategy) እነሱ ብቻ ባለ ሀብት የሚሆኑበትን ስርአት ዘርግተዋል፡፡ አብዛኛዉ ሕዝብና በተለይም ወጣቱ የእድገትና ሠርቶ የመኖር በሮቹ ሁሉ ተዘግተዉበት ለጦርነትና ለአጉል ሱስ ወይንም ለቦዘኔነት ተማግዶ የኑሮ አዘቅት ዉስጥ ወድቋል፡፡ ወያኔ ለሕዝቡ ዕድገትና የኑሮ መሻሻል የሚታይበት ቀን እንዳይመጣና ሕዝቡ ተደራጅቶ የጭቆና ቀንበሩን እንዳይወረዉር ለሁሉም ድርጅቶችና ፓርቲዎች ተጻራሪ ወይም ተለጣፊ በመፍጠር ከፋፍለህ ግዛዉ በሚለዉ መ ርህ ሕዝቡን በመበታተን ላይ ይገኛል፡፡

ሽምግልና በባህልና በእዉነተኛ ትርጉሙ ሁለት ተጻራሪ ጎራዎች በሕግም ሆነ በራሳቸዉ ፈቃድ መስማማት ሳይችሉ ሲቀሩ በመሃል በመግባት ለሁለቱም ጥቅምና ጉዳት ላይ በመመርኮዝ በቅንነትና ሳያዳላ መፍትሄ የሚሰጥበት ሂደት ነዉ፡፡ ታዲያ ይህን ያህል ታላቅ ሂደት የሚያከናዉኑ ሰዎች ብቃትና ተቀባይነት ያላቸዉ፣ ሰዉን በሰዉነቱና በወገናዊነቱ የሚያከብሩ፣ ለወደፊቱ ትዉልድ የሚ ገዳቸዉ መሆኑ ይገባቸዋል፡፡ በሽምግልና ስም የራስን አላማና የሌላ ተልኮን ለማሳካት መሞ ከር ግን በወገን ላይ ግፍ መስራት ከመሆኑ ባሻገር በእግዚአብሔርም ሆነ በሰዉ ዘንድ ያስጠይቃል፡፡ ለምሳሌ የቅንጅትን ታሪክ ብንመረምር ዉህደቱን ለማምጣት በነበረዉ ከፍተኛ አለመግባባትና መሠረታዊ ልዩነቶች ሳብያ ቁጥር ስፍር የሌላቸዉ ሽምግልናዎች ተካሂደዉ ነበረ፡፡ ሽምግልናዉ ግን ዉህደቱን ቢያመጣም ከላይ የተጠቀሱትን ባህሪያት ያላሟላ ስለነበር በዉህደት ፋንታ የተካሄደዉና የተሞከረዉ ስለልጣንና የሕዝብ ተቀባይነትን የመዝረፍ ወይም የመቀማት ሴራ ነበር፡፡ መሪዎችም በእስር ቤት እያሉ በሽምግልና ስም እነ ፕሮፌሰር ኤፍሬም ለወያኔ ምን ሚና እንደተጫወቱ ያደባባይ ሚስጥር ነዉ፡፡

አሁንም ዛሬ ሽምግልናን በመሠረታዊ አላማዉ ሳይሆን ለወያኔ ዕድሜ ማራዘሚያና እጅ መንሻ እንዲሆን እንደ አንድ መሣሪያ ለመጠቀም የሚራወጡ አካሎች አሉ፡፡ በእርግጥ የኢትዮጲያን ችግር አንድ ወይም ሁለት ፓርቲ

ይወጣዋል ብሎ ማመን ያስቸግራል፣ ለዚያ ሕዝብ ግን ምህረትን ለማምጣትን ነፃነቱን ለማዉረስ ሀይልን ማጠናከርና ወደ አንድ መምጣት አስፈላጊ ቢሆንም ዉህደታችን የዉሃና የዘይት ሆኖ ዉጤት ከማስመዝገብ ይልቅ ትግሉን የሚበትንና ልዩነትን የሚያሰፋ እንዳይሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ ትክክለኛዉን ዉህደት አምጥቶ ለድል ለመብቃት የፓርቲዎች ጥራትና የሕዝብ ተቆርቋሪነት እየተመዘነ በመሰባሰብ ሕዝብ የሚመደግፈዉ ታላቅ ፓርቲ መፈጠር ይኖርበታል፡፡ ወደፊትም አብሮ ለመሥራትና ለድል ለመብቃት የትግል አላማ አንድ መሆን፣ ተቆርቋሪነትና መስዋትነት፣ የዉጪና የዉስጥ ጠላትና ወዳጅን መለየት፣ የሰዎችን ባህሪን መመርመር ይጠይቃል፡፡ ይህንንና ይህንን የመሳሰሉ ጉዳዮች ሽምግልናን ዉስብስብና ብስለትን የሚጠይቅ ረቂቅ ጉዳይ ስለሚያደርጉት በቀላሉ መልስ ለማግኘት ያዳግታል። እነዚህንም በደንብ ተረድቶ መንቀሳቀስ ድግሞ ዉጤታማ ለመሆን ያስችላል፡፡ ለኢትዮጲያ ትግል እንቆማለን፣ እንታገላለን የሚል ወገን ሁሉ እንዲህ ዓይነቱን ጥፋት በየዋህነትም ሆነ በመሰሪነት የሚያከናዉኑ ክፍሎች ስላሉ ከእንዲህ ዓይነቱ የወገን በደል ተጠያቂነት ለመዳን ድረ ገፆችም ሆነ ግለሰቦች ጥንቃቄ እንዲያደርጉ አደራ እላለሁ፡፡

ኢትዮጲያና ሕዝቦችዋ በአንድነት ለዘላለም ያሸንፉሉ!

[1] The End of History and Last Man (1992) By Francis Fukuyama